Baankii Hojii Gamtaa Oromiyaa
የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ

# ለኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 19ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ቅዳሜ ታህሳስ 6 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በአዳማ ከተማ፣ አባ ገዳ አዳራሽ ያካሂዳል፡፡ ስለሆነም ባለአክሲዮኖች በተጠቀሰው ቦታ፣ ቀንና ሰዓት ተገኝታችሁ የጉባኤው ተሳታፊ እንድትሆኑ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 366 (1)፣ 367 (1)፣ 370 እና 371 (1) እንዲሁም በባንኩ መመሥረቻ ፅሑፍ አንቀፅ 17(1) እና 18(1) መሠረት ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

## የጉባኤው አጀንዳዎች

1. የጉባዔውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣
2. እ.ኤ.አ. ከህዳር 24/2022 እስከ ህዳር 30/2023 ድረስ የተደረጉትን የአክሲዮኖች ዝውውር እና የባለአክሲዮኖችን ብዛት ማሳወቅ፤
3. እ.ኤ.አ. የ2022/23 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥ፤
4. እ.ኤ.አ. የ2022/23 የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥ፣
5. ከላይ በተራ ቁጥር 3 ሥር በቀረበው አጀንዳ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
6. ከላይ በተራ ቁጥር 4 ሥር በቀረበው አጀንዳ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
7. እ.ኤ.አ. በ2022/23 ሒሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
8. እ.ኤ.አ. የ 2022/23 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ክፍያን እና የ2023/24 ወርሃዊ አበል መወሰን፤
9. እ.ኤ.አ. ለ 2023/24 የውጭ ኦዲተሮችን መሾም እና ክፍያቸውን መወሰን፤
10. የተሻሻለውን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ መመሪያን ማጽደቅ፤
11. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ክፍያን መወሰን፤
12. የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫን ማከናወን፤
13. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ፡፡

## ማሳሰቢያ፡-

1. ባለአክሲዮኖች ወይም ተወካዮች በጉባኤው ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው መሆኑን ወይም ትውልደ-ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውን እና አንድ ኮፒ መያዝ ያለባቸው መሆኑን፤
2. በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕጉ አንቀፅ 377 (1) መሠረት አዲስ አበባ፣በሌ መንገድ በሌ ሩዋንዳ አከባቢ፣ ራንግ ህንፃ፣9ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የባንኩ አክሲዮን አስተዳደር ክፍል ወይም በአቅራቢያቸው በሚገኘው የባንኩ ቅርንጫፍ በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የውክልና መስጫ ቅጽ በመሙላት በተወካያቸው ተገኝተው መሳተፍ እና ድምፅ መስጠት የሚችሉ መሆኑን፤
3. ድርጅትን (የኅብረት ሥራ ማኅበርን ወይም ሌላ ድርጅትን) ወክሎ የሚቀርብ ተወካይ የድርጅቱ/የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ/ሊቀመንበር መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዞ መቅረብ ያለበት መሆኑ፤አለዚያም በባንኩ የውክልና መስጫ ቅጽ መሠረት ውክልና የተሰጠው መሆኑን፣
4. ከላይ በተራ ቁጥር 2 እና 3 ሥር ከተመለከቱት ውጭ በውክልና በስብሰባው ላይ ለመገኘት የሚፈልጉ ካሉ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል የተሰጠ በጉባኤው ለመሳተፍ እና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ሰነድ ዋናውንና ኮፒውን ይዘው መምጣት ያለባቸው መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

**ይህ ማስታወቂያ እስከወጣበት ቀን፡- የተፈረመ ካፒታል ብር12,282,459,400.00፤የተከፈለ ካፒታል ብር 10,119,587,100.00**

# የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ

+251 115 15 02 29
+251 115 58 24 51
info@coopbankoromia.com.et
የፖስታ ሳጥን ቁጥር 16936
ዋና መ/ቤት አድራሻ፡- አዲስ አበባ፣ በሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 02፤
የቤት ቁጥር፡-አዲስ
የንግድ ምዝገባ ቁጥር፡- KK/AA/3/0001918/2004፤
የሥራ ፈቃድ ቁጥር፡-LLB/008/2004;
609 የጥሪ ማዕከል
www.coopbankoromia.com.et